ኢ ኤስ ግራዝሚክ ማርቲን

*የስቴቱ ትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ*
*አገረ ገዢ*

Maryland State Department of Education
Division of Special Education/Early Intervention Services
200 W. Baltimore Street, Baltimore, MD 21201
www.marylandpublicschools.org

COMMUNITY MEDIATION MARYLAND
*your conflict, your solutions*

# ሜሪላንድ ውስጥ በአወያይ አማካኝነት የሚደረጉ የ IEP ቡድን ስብሰባዎች

## ለወላጆችና ለሕዝብ ድርጅት/የትምህርት ቤት ሠራተኞች የተዘጋጀ መግቢያና ባብዛኛው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

<u>በአወያይ አማካኝነት የሚደረጉ የIEP ቡድን ስብሰባዎች መግቢያ፦</u> የውጪ፣ የግልና ተገቢውን ሥልጠና ያገኘ "አወያይ" በ IEP ቡድን ስብሰባዎች ላይ ተገኝቶ ወላጆችና የትምህርት ቤት ሠራተኞች ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች ለሚያስፈልጋቸው ወይም ያስፈልጋቸዋል ተብሎ ለሚታመኑ ተማሪዎች ትምህርት ነክ ውሳኔን በተመለከተ ስምምነት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ በይበልጥ ዝነኛ የሆነ መንገድ እየሆነ መጥቷል። በወላጆችና በትምህርት ቤት ሠራተኞች መካከል ያለው ግንኙነት ከመሻከሩ በፊት ወይም ግንኙነቱ ጠብ ላይ ከመድረሱ በፊት፣ ወላጆችና የትምህርት ቤት ሠራተኞች የውጪ አወያዮችን መጠቀም ለ IEP ቡድን ሂደት ጠቃሚ እንደሆነ እያገኙት ነው። ስብሰባው ልያ የሚኪያሂዱ ውይይቶች አስቸጋሪ እንደሚሆኑ ከታመነ፣ ወላጆችና የትምህርት ቤት ሠራተኞች አለመግባባቶችንና አለመስማማቶችን እንዳይኖርባቸው አንድ አወያይ ሊረዳ ይችላል። መጠቀም የ IEP ቡድኖች ከአለመግባባት የሚመጡ ግጭቶችንና አለመስማማቶችን እያስተናበሩ የተማሪው የትምህርት መርሀ ግብር ማደራጀት ላይ እንዲያተኩሩ ተገቢውን ሥልጠና ያገኘ አወያይ መጠቀም ውጤታማ መንገድ ሆኖ ተገኝቷል። አወያዩ ስልቶቹን ተጠቅሞ፣ የ IEP ቡድን አባሎች፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞችና ወላጆች ተደማምጠውና አካለስንኩልነት ላላቸው ወይም አለባቸው ተብለው ለሚጠረጠሩ ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የትምህርት መርሀ ግብሮች ለማዘጋጀት አብረው እንዲሠሩ የሚያስችል ሁኔታ ይፈጥራል።

1. **የIEP ስብሰባ አወያይ እንዲኖረው ማን መጠየቅ ይችላል?**

   ወልጁ ወይም ትምህርት ቤቱ አወያይ መጠየቅ ይችላል። ሆኖም ይህንን በፈቃደኝነት የሚደረግ ሂደት ለመጠቀም ሁለቱም ወገኖች መስማማት አለባቸው።

2. **የIEP ስብሰባ አወያይ ሆኖ የሚያገለግለው ማነው?**

   አወያዩ ሥልጠና የወሰደና በፈቃደኝነት የሚሠራ ሲሆን የሚመጣውም ወላጁ ከሚኖርበት አውራጃ ውስጥ ወይም ሌላ ወላጁ ከሚኖርበትና ልጁ ትምህርት ቤት ከሚሄድበት አካባቢ ቅርብ የሆነ ማህበረሰብ የሚገኝ የማህበረሰብ የግልግል መዓከል ነው። አወያዩ 50 ሰዓት የሚፈጅ የግልግል ስልቶች ክፍል ወስዶ የጨረሰ፣ በተለያዩ አለመግባባቶች ላይ የገላጋይነት ልምድ ያለውና የ 3 ቀን የ IEP አወያይነት ሥልጠና የወሰደ ነው። አወያዩ የ IEP ቡድን አባል አይደለም እንዲሁም ከትምህርት ቤቱ ወይም ከወላጆች ጋር ስብሰባው ላይ ከመርዳት

ውጪ ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም። አወያዩ ገለልተኛ ሆኖ ይቆይና ቡድኑ ውሳኔዎች እስከሚያደርግ ድረስ ሂደቱ ላይ አተኩሮ ይቆያል።

3. በአካለስንኩላን ግለሰቦች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) መሠረት አወያይነት ከግልግል በምን ይለያል?

በአወያይ አማካኝነት የሚደረጉ የ IEP ቡድን ስብሰባዎች ግጭቶችን ለማስቀረት እና/ወይም ግልግልን ከመጠየቅ በፊት ወይም የፍትህ ሂደት አቤቱታ ከማስገባት በፊት ግጭቶችን ለመፍታት መጠቀም እየታወቀ የመጣ መንገድ ቢሆንም በ IDEA ሥር ግን አስፈላጊ አይደለም። ስቴቶችና የአካባቢው የትምህርት ሥርዓቶች አገልግሎቱን የመስጠት ግዴታ የለባቸውም። በIDEA ሥር በIEP አወያይነትና በግልግል መካከል ያሉ ሌሎች ልዩነቶች የሚከተሉት ናቸው፦

- አወያይነቱ የሚከሰተው የ IEP ቡድን በተለምዶ ከሚያደርገው ስብሰባ ላይ ነው
- የ IEP ስብሰባው በአጠቃላይ የሚመራው፣ ልክ አወያይ የሌለበት የ IEP ስብሰባ በሚመራበት መንገድ በትምህርት ቤቱ ሥርዓት ነው
- ለተማሪው በጽሑፍ ከቀረበው የግል የትምህርት መርሀ ግብርና ቀደም ብሎ የ IDEA አስፈላጊ ማስታወቂያ በስተቀር የጽሑፍ ስምምነት የለም።

የIEP አወያይነትና ግልግል መምታታት የለባቸውም። ከ IEP ስብሰባ ውስጥ ይልቅ በይበልጥ ስፋት ያላቸው የተለያዩ የልዩ ትምህርት ጉዳዮችን ለማስተናበር ግልግልን መጠቀም ይቻላል። ግልግል በተለምዶ የሚጠቀሙት፣ ሁለቱ ወገኖች በሌላ መንገድ መፍታት የማይችሉት ትልቅ አለመግባባት ሲኖር ነው። ሥልጠና ያገኘና ወገን ሳይዝ የሚቀርብ ገላጋይ ሁለቱ ወገኖች የተለያዩ አለመስማማቶችን እንዲፈቱ ያገናኛቸዋል፣ ብዙውን ጊዜ ከተማሪው IEP ውጪ የሆኑትን አለመስማማቶችን ጨምሮ።

4. አወያዩ ስብሰባው ላይ ምን ያደርጋል?

አወያዩ የሚከተሉት ይጠበቅበታል፦

- ቡድኑ የመወያያ ነጥቦች እንዲያወጣ መርዳት
- ውይይቱን መንገድ እያስያዘ ትኩረቱን ተማሪው ላይ ማቆየት
- ሁሉ ሰው የመናገርና የመሰማት እንዲኖረው ማድረግ
- አለመስማማቶችን ለመፍታት መርዳት
- የንግግር ስልቶችን በመጠቀም ወላጆችና የትምህርት ቤት ሠራተኞች አብረው እየሠሩ ስለ መርሀ ግብሩ ውሳኔዎች እንዲያቀርቡ መርዳት
- የቡድን አባሎች ከዚህ በፊት የተከሰቱ ጉዳዮችን በተመለከተ ግልጽ የሚያደርጉ ጥያቄዎች አዘጋጅተው እንዲጠይቁ መርዳት
- ቡድኑ ሥራው ላይ አተኩሮ ለስብሰባው በተመደበለት ጊዜ ውስጥ እንዲጨርስ መርዳት
- ገለልተኛ ሆኖ፣ ወገን ሳይዝ፣ ማንንም ጥፋተኛ ሳያደርግ፣ ቡድኑ ላይ ውሳኔ

ሳያስገድድ ወይም ስለ ውሳኔው ተገቢነት የግል ሓሳቡን ሳያቀርብ መቆየት።

5. በአወያይ አማካኝነት የሚኪያሄድ የ IEP ቡድን ስብሰባ ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

በአወያይ አማካኝነት የሚደረጉ ስብሰባዎችን ያኪያሄዱ ወላጆችና የትምህርት ቤት ሠራተኞች የሚከተሉትን ያገኟቸውን ጥቅሞች ዘገባ አቅርበዋል፦

- ትኩረቱ ተማሪው ላይ ሆኖ ይቆያል
- ሁሉም ወገኖች በተሟላ ሁኔታ እንዲሳተፉ ድጋፍ ያቀርባል
- በወላጆችና በትምህርት ቤት ሠራተኞች መካከል ያለው የሥራ ግንኙነት ጥሩ ሆኖ ይቆያል
- ለየት ያሉ ለሁሉም አሸናፊ የሆኑ መፍትሔዎች የመፍጠርና የማግኘት ዕድል አለ
- የአወያይ አገልግሎቶች ለወገኖች በነጻ የሚሰጡና ፊት ለፊት መጋፈጥ ሳይኖር የሚደረጉ ናቸው
- ውጤታማ የሆኑ የንግግርና የማዳመጥ ስልቶች ይከተላሉ
- የመስማማትና ያለመስማማት ነጥቦች በግልጽ ይነገራሉ
- ወላጆችና ባለሙያዎች ያልተፈቱ ችግሮችን ለማስተናበር አዳዲስ አማራጮች እንዲያሳውቁ ይበረታታሉ
- ሁልጊዜም ከሚደረገው የ IEP ስብሰባ ክፍል ስለሆነ የተለየ ስብሰባ አያስፈልገውም
- ውሳኔዎች ሁሉ በቡድኑ እንጂ በገላጋይ ወይም በይግባኝ ባለሥልጣን አይደረጉም

6. የተማሪውና የቤተሰቡ መረጃ በምስጢራዊነት የሚያዘው እንዴት ነው?

ትምህርት ቤቱ ስለ ተማሪው በምስጢር የተያዘን መረጃ ከአወያዩ ጋር እንዲያካፍል ወላጅ ፈቃዱን መስጠት አለበት። ይህ በቤተሰብ ትምህርት መብትና የመረጃው ምስጢራዊነት ድንጋጌ መሠረት አስፈላጊ ነው።

7. አወያዩን የሚከፍለው ማነው?

አወያይ የ IEP ሂደት ላይ ሲረዳ ወላጁ ወይም ትምህርት ቤቱ ምንም ወጪ የለባቸውም። አወያዮቹን ለማሠልጠንና መርሀ ግብሩን ለመደገፍ፣ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ አወያዮቹ መኪና ሲነዱ ለቤንዚን የሚያወጡትን ገንዘብ ለመተካት የሚጠቀሙት ገንዘብ የሚመጣው በተከበሩት ዋና ዳኛ ሮበርት ኤም ቤል፣ የሜሪላንድ የይግባኞች ፍርድ ቤት፣ እና የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች፣ ኬሮል አን ባግሊን፣ Ed.D፣ ረዳት ስቴት ዋና ተቆጣጣሪ አመራር ሥር ባለው የስቴት የፍትህ አካል ግልግልና የአለመግባባት መፍቻ ቢሮ (State Judiciary's Mediation and Conflict Resolution Office) ለሜሪላንድ የማህበረሰብ ግልግል (Community Mediation Maryland) በሚሰጠው ገንዘብ ነው።

8. ለወላጆችና ለትምህርት ቤት ሠራተኞች በአወያይ አማካኝነት የሚደረጉ ስብሰባዎችን የሚሰጡ የሕዝብ ድርጅቶች የትኞቹ ናቸው?

የሚከተሉት የሕዝብ ድርጅቶች በ2007-2008 የትምህርት ዓመት ውስጥ ለወላጆችና ለትምህርት ቤት ሠራተኞች የአወያይ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፦

- Anne Arundel County Public Schools (አን አሩንዴል አውራጃ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች)
- Baltimore County Public Schools (ባልቲሞር አውራጃ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች)
- Cecil County Public Schools (ሴሲል አውራጃ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች)
- Board of Education for Dorchester County (የዶርቼስተር አውራጃ የትምህርት ኮሚቴ)
- Frederick County Public Schools (ፍሬዴሪክ አውራጃ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች)
- Howard County Public Schools (ሃወርድ አውራጃ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች)
- Montgomery County Public Schools (ሞንትጎመሪ አውራጃ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች)
- Prince George's County Public Schools (ፕሪንስ ጆርጅ አውራጃ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች)
- St. Mary's County Public Schools (ሴንት ሜሪ አውራጃ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች)
- Washington County Public Schools (ዋሽንግተን አውራጃ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች)

አወያዮቹና አገልግሎቶቹ የሚቀርቡት በሚከተሉት የማህበረሰብ የግጭት መፍቻ ማዕከሎች ሠራተኞችና በፈቃደኝነት በሚሠሩ ሰዎች ትብብር ነው፦ *Anne Arundel Conflict Resolution Center(አን አሩንዴል የአለመግባባት መፍቻ ማዕከል)፣ Charles County Community Mediation Center (ቻርልስ አውራጃ የማህበረሰብ ግልግል ማዕከል)፣ Mid-Shore Community Mediation Center(ሚድ ሾር የማህበረሰብ ግልግል ማዕከል)፣ Washington County Community Mediation Center(ዋሽንግተን አውራጃ የማህበረሰብ ግልግል ማዕከል)፣ Conflict Resolution Center of Montgomery County(የሞንትጎመሪ አውራጃ የአለመግባባት መፍቻ ማዕከል)፣ Community Mediation, Upper Shore, Inc(አፐር ሾር የማህበረሰብ ግልግል)፣ Center for Conflict Resolution, Inc.*, Salisbury(ሳሊዝበሪ የአለመግባባት መፍቻ ማዕከል)፣ *Prince George's County Mediation and Conflict Resolution Collaborative(ፕሪንስ ጆርጅ አውራጃ ግልግልና የአለመግባባት መፍቻ ትብብር)፣ Community Mediation Center of St. Mary's County(የሴንት ሜሪ አውራጃ የማህበረሰብ ግልግል ማዕከል)፣* እና የ *Community Mediation Maryland (የሜሪላንድ ማህበረሰብ ግልግል) ሠራተኞች፣* በዋና ሥራ አስኪያጅ በሎሪግ ቻርኮዲያን፣ Ph.D.፣ *አመራር ሥር ነው።*

**9. ለልጄ የሚደረገውን የ IEP ቡድን ስብሰባ አወያይ እንዲሳተፍበት ከፈለግሁ ማንን ነው የምገናኘው?**

የአወያይ አገልግሎቶች የሚሰጡ የትምህርት ሥርዓቶች አወያይ የሚጠየቅበትን መንገድ እያንዳንዳቸው ለብቻ አድርገውታል። አገልግሎቱን እንዴት መጠየቅ እንደሚችሉ ለማወቅ ለልጁ የትምህርት መርሀ-ግብር ኃላፊ በሆነው የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የሚገኘውን የልዩ ትምህርት ዋና ሥራ አኪያጅ ቢሮ በመገናኘት ወይም የሜሪላንድ ማህበረሰብ ግልግልን በስልክ (410-349-0080) በመናኘት ነው።

**10.የእኔ የትምህርት ሥርዓት በአወያይ አማካኝነት የሚደረጉ የ IEP ቡድን ስብሰባዎች የማይሰጥ ከሆነ ማንን ነው የምገናኘው?**

**የትምህርት ሥርዓትዎ በአወያይ አማካኝነት የሚደረጉ የ IEP ቡድን ስብሰባዎች እንዲሰጥ የሚፈልጉ ከሆነ የአካባቢውን የትምህርት ሥርዓት የልዩ ትምህርት ዋና ሥራ አስኪያጅ መገናኘት አለብዎት። የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍልና የሜሪላንድ ማህበረሰብ ግልግል፣ አገልግሎቱን ለአካለስንኩል ተማሪዎች ወላጆችና ለትምህርት ቤት ሠራተኞች መስጠት ለሚፈልጉ የትምህርት ሥርዓቶች ሁሉ ለማስፋፋት በትጋት ይሠራሉ። መስጠት የሚችሉት በተገኘው የሠለጠኑ አወያዮች ቁጥር ልክና የሜሪላንድ የማህበረሰብ ግልግልና እያንዳንዱ የአለመግባባት መፍቻ ማዕከል እንደቻሉት መጠን ነው።**

**በአወያይ አማካኝነት የሚደረጉት የIEP ስብሰባዎች እንደማንኛውም ሌላ የ IEP ስብሰባ አንድ ዓይነት መሆናቸውን ማወቅ አስፈላጊ ነው። የሕግ ደንቦችን ማክበርና ማንኛውንም ሌሎች በሜሪላንድ ውስጥ የ IEP ሂደትን የሚያስተዳድሩ አስፈላጊ ነገሮችን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል። ዋናው ትልቅ ልዩነት የአወያይ መገኘት ነው።**

*MSDE ይህንን ሰነድ ሲያዘጋጅ የኖርዝ ካሮላይና የሕዝብ ትምህርት ክፍል፣ ልዩ ልጆች ክፍልና የልዩ ትምህርት ተገቢ አለመግባባት መፍትሔ ትብብር (CADRE)እርዳታ ስላቀረቡ ሊያመሰግን ይፈልጋል።*

*የገንዘብ ድጋፍ የቀረበው በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ከ IDEA ክፍል B ችሮታ #HO27A070035A፣ የዩ ኤስ የትምህርት ክፍል፣ የልዩ ትምህርትና መቋቋሚያ አገልግሎቶች ቢሮ በኩል ነው። በዚህ ውስጥ የተገለጹ አስተያየቶች የዩ ኤስ የትምህርት ክፍልን ወይም ማንኛውም ሌላ የፌዴራል ድርጅትን ወክለው አይደለም እንደሱም መታየት የለባቸውም። የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው ከልዩ ትምህርት መርሀ ግብሮች ቢሮ፣ ከልዩ ትምህርትና መቋቋሚያ አገልግሎቶች ቢሮና ከዩ ኤስ የትምህርት ክፍል ነው።* *ይህ መረጃ ከሕትመት ሕግ (ኮፒራይት) ነጻ ነው። አንባቢዎች አባዝተው እንዲጋሩት ይበረታታሉ ሆኖም ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ አገልግሎቶች መምጣቱን እባክዎን ያስታውቁ።*

*የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ሥራ ቅጥርን ወይም በአንዳንድ የመርሀ-ግብር ተሳትፎዎችን በተመለከተ ተጻዕኖ ሊያሳድር የሚችል በጎሳ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በብሄር፣ በሃይማኖት ወይም በአካለ ስንኩልነት ላይ የተመሠረተ ምንም ዓይነት አድሎ አያደርግም። የክፍሉን አመራር በተመለከተ ጥያቄዎች ካልዎት የእኩልነት ማረጋገጫና መፈጸሚያ ቅርንጫፉን (Equity Assurance and Compliance Branch) በስልክ ቁጥር (410)767-0433 በመደወል ወይም በፋክስ ቁጥር (410)767-0431 መገናኘት ይችላሉ። የአካል ጉድለት ያለባቸው አሜሪካዊያን (Americans with Disabilities Act (ADA)) በደነገገው መሠረት ይህ ሰነድ በተጠየቀ ጊዜ በአማራጭ አቀራረቦች ዝግጁ ሆኖ ይገኛል። የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚገኘውን የልዩ ትምህርት/ቅድመ ገላጋይ አገልግሎቶችን ክፍል በስልክ ቁጥር (410)767-0858 ወይም በፋክስ (410)333-1571 ይገናኙ።*

*Dev. 08/2007*